# አልነጋም- ገና ነው!



የሰማይ ኮርኔሥ ሆኖ- ማቅ የመሰለ ደመና

ከታችም አውሎ ነፋስ- ፉጨቱን እያሰማ

አቧራውን አሥነስቶ- ዛፍ ቅርንጫፉን እያሾረ

ዛሩ እንደወረደ ባለአውሌ- አለመጠን እያስጨፈረ

አይን ቢወጉ በማያሳይ- ጥቅጥቅ ባለ ጨላማ

ወዴት ነው መድረሻችን- ጉዟችን የሚያቀና?

        ትናንት እንዳስቀመን ዝናብ- ሊዘንብ  ሰማዩ አግቶ

        ወዴት ነው የምንሄደው- በትናንቱ ምን ታይቶ?

ትርምስምሳችን ወጥቶ- ጨቅይቶ ሳለ መንገዱ

ለይምሰል አይሆንምወይ -ደግመን ዛሬ መሄዱ?

        ትናንት መካሪ ጠፍቶ- ሌሊቱ ገና እናዳልነጋ

        ጉዞው መርዛም-እሾክ በዝቶበት- ስንቱ ነው የተወጋ?

እኔስ አልምክርውም- የዛሬውን መንገድ

እስኪነጋ እቀያለሁ- ካልሆነብኝ የግድ

አልነጋም ገና- ጨለማ ነው ሌሊት

እነሱንም ንገሩዋቸው- መኳዙን ይተውት

ተከታያቸውን በመሉ- የአውሬ ቀለብ አያርጉት።


ዳግማዊ ዳዊት

Ethio_dagmawi@yahoo.com


ጥር 2002 ዓ.ም.